# (AFD) የተሰኘውን ስብስብ በለንደን ለምን መቃወም አስፈለገ ?

ለንደን ለምንገኘው ኢትዮጵያውያን የወገናዊነት ሰላምታችንን በማስቀደም “ስብስብ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ(AFD)”የተሰኘውን ለምን እንደምንቃወም ለማሳወቅ ለማንበብ ጊዜ እንዲኖራችሁ በማሰብ እያከታተልን አጫጭር ጽሑፎች ልናቀርብላችሁ ቃል እንገባለን።

በዛሬው እለት እናንተው አንብባችሁ አገራችንን ለማዳን ትችሉ ዘንድ አንዳንድ ውሎችን እንጠቋቁማችኋለን።ራሳችሁም በጥሞና እንድትጠያየቁበት በሃገር ወገን ስም አደራ እንላችኋለን።እኛም እንደናንተው የሃገር፤ወገን የዘላቂ ጥቅም እንጂ፤ ለግል ክብርና ጥቅም የምንዶልት እንዳልሆነ ልቦናችሁ ያውቃል።

- ጃንሆይ ተጠሉ ተባለ፤ወረዱ።ኢትዮጵያና ልጆቿ ምን ተጠቀሙ፤ተጠቀምንስ?
- መንግስቱም እንደዚሁ።እምዬ ምን ተጠቀመች? እኛስ ልጆቿ?
- መለስም መጣ፤የባሰ አታምጣ!

አሁን AFD የሚሰኘውን የምንቃወመው ሰዎች መለስን ለመቃወም ከማንም ያላነሰ የተቃወምንና አሁንም እንደምንቃወመው እናንተው ምስክሮች ናችሁ። ለእሁዱ የAFD ስብሰባም አትግቡ አላልንም።አልወጣንም።በዚያ ስብሰባ ላይ የኦነግ ፤ የሻብያ፤የሌሎች ተነጣዮች ተሰግስገው ለጥያቄና ትችት በአንድና በሁለት ደቂቃ ተወስናችሁ፤ ለነሱ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ እንዳትሆኑ ለማስጠንቀቅ ብቻ ነው።

Memorandum of Association የተባለውና Statutes of the Alliance for Freedom and Democracy (AFD)/Press Release (May 29,2006) ተጥላቻ ከባሰ ገደል ውስጥ እንዳይጨምረን አጥብቀን መጠንቀቅ አለብን።የመጀመሪያው ለ17 አመታት አማቀቀን።ሁለተኛውም እንደዚህ፤እንድያውም በባሰ ሁኔታ።ሶስተኛውና “መጭው” ካለፉት ብሶና ረዝሞ ምናልባትም እናት አገራችንን “The Former Ethiopia” እኛው እንዳናደርጋት እንጠንቀቅ።

መስከረም 21 ቀን በተደረገው ስብሰባ ለንደን የምንገኘው ኢትዮጵያውያን እንደተለመደው ታሪክ አስመዝግበናል።በዚያን እለት ለናንተ ለኢትዮጵያ ልጆች ፍርድ እንቀርባለን ያልነው የቅንጅት መሪዎችን እነዚሁ የአለም አቀፍ የቅንጅት መሪዎች ነን የሚሉት እስከ እድሜ ልክ ጥብቅ እስራት የተጣሉበትን ማስረጃዎች፤ አሁን ባሉባቸውም ሁኔታዎች እንዴት እንዳስጠበቁባቸው፤የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ነን ብለው ይህን ሁላ የፈፀሙት፤የሚፈፅሙት የማእከላዊ ኮሚቴ አባል እንዳልሆኑና ሊሆኑም እንደማይችሉ ማስረጃ ለማቅረብ፤-ኢሳያስ፦ *ከ10 አመት በኋላ እትዮጵያ የምትባል አገር አትኖርም! ያለውን በምን አይነት እየፈፀሙ እንደሆነ ማስረጃዎች በአንዳንድ ሰዎች ስለ አርበኞች ግንባር(EPPF) ፤በተጨማሪም ከአርበኞች ግንባር መሪዎች አንዱ የነበሩ አሁን ከአስመራ መጥተው ኢትዮጵያን ሊያጠፏት ነው።ዝም ትላላችሁ? እያሉ የሚንገበገቡትን እና ውዱ አርቲስት ሰለሞን ተካልኝን ለናንተው ማስረጃነት እናቀርብላችኋለን።*

እስከዚያው ወገኖች ሆይ! መጠቀሚያ እንዳትሆኑ በእናት ኢትዮጵያ ስም እንደገና አደራችንን እናጠብቃለን።

ፈጣሪ አምላካችን ኢትዮጵያን ይጠብቅልን።

አሜን